# Learning by Ear 2013

«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»

EPISODE 13: «አዲሱ መኖሪያዬ»

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ትዕግስት MOVES IN WITH ምኞቴ**

- **ምኞቴ (M, 35)**
- **ትዕግስት (F, 15)**

**SCENE 2: AT THE JUMBES’**

- **ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE 3: ዳንኤል IN በለጠ’S ROOM AT NIGHT**

- **በለጠ (M, 16)**
- **ዳንኤል(M, 16)**

**SCENE 4: MORNING AT THE MSOTOS’**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**INTRO**

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን! ይህ መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–መዘዙን መቀበል” የተሰኘው ድራማ ቀጣይ ክፍል ነው። በዚህ የሬዲዮ ድራማ ንጉሴን፣ ዳንኤልን እና ምህረትን ጨምሮ የጥቂት ታዳጊ ወጣት አፍሪቃውያንን የዕለት ከለት ኑሮ ለመዳሰስ ሞክረናል። እነዚህ ሶስት ወጣቶች ርዕሰ መምህራቸው ሰብለ ቢሮዋቸው ጠርተው ካነጋገረቻው በኋላ ሠማይ ምድሩተገላብጦባቸዋል:

## 2. EPISODE 12, LINES 85 – 91:

***JULIETTE:*** *ጥሩ ከንጉሴ እንጀምር. (…)ማሪዋና ብቻ አይደለም የሚያጨሰው አልኮልም ይጠጣል። የምትለው ነገር አለህ ንጉሴ?*

*ንጉሴ:የለም መምህርት!*

***JULIETTE:****(…)በቅርቡ ዳንኤል እና ምህረት ባልና ሚስት ሆነው ሲጫወቱ ነበር። አሁን ይሄው የመጀመሪያ ልጃቸውን እየጠበቁ ነው።! (…)* ***91.*** *(…)ሶስታችሁም ከቦንጎ አካዴሚ ተባራችኋል።*

## 3. NARRATOR:

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእነሱ የክፍል ልጅ ትዕግስት ከቀድሞ ፍቅረኛዋና የታክሲ ረዳቱ ምኞቴ የሚገርም ጥያቄ ቀርቦላታል- እሱ  ጋ ጠቅልላ በመግባት አብራው እንድትኖር እንደሚፈልግ ነግሯታል! ግን የምኞቴ ዋነኛ ምክንያት ፍቅር አይደለም። የታመሙት እና በእድሜ የገፉት እናቱ ናቸው እንዲያገባ የሚገፋፉት።:

## 4. EPISODE 7, LINE 65:

***MABEL:*** *እሺ ምኞቴ። በል እስቲ ንገረኝ። መቼ ነው የምታገባውና የልጅ ልጆች የማየው?*

## 5. NARRATOR:

እንግዲህ ዘና በሉ ተቀመጡና የዛሬውን «አዲሱ መኖሪያዬ» የተሰኘውን 13ኛ ክፍል ድራማ አድምጡ። ምኞቴ ለትዕግስት በጣም የሚያምር አካባቢን እያሳያት ነው…

**SCENE 1: ትዕግስት MOVES IN WITH ምኞቴ**

**6. ATMO: EVENING IN A MIDDLE CLASS AREA, NOT SO NOISY. INTERIOR**

**7. SFX: DOOR OPENS**

**8. SFX: FOOTSTEPS - TWO PEOPLE**

**9. ምኞቴ:** ይኸው እንግዲህ፤ ወደ አዲሱ መኖሪያ ቤትሽ እንኳን ደህና መጣሽ ትዕግስት። ወይንስ ወይዘሮ ትዕግስት ልበል? … አባባሉን እንዴት አገኘሽው፤ ወይዘሮ ትዕግስት?

**10. ትዕግስት:** **(laughs)** በጣም ነው ደስ ያለኝ አቶ ምኞቴ።

**11. ምኞቴ:** እንግዲህ ይሄው ሻንጣሽ።…

**12. SFX: BAG PUT ON FLOOR**

**13. ትዕግስት:** ለሸክሙ አመሰግናለሁ።

**14. ምኞቴ:** ምንም አይደል። ሌላ የማደርግልዎ ነገር አለ ወ/ሮ ትዕግስት? ምናልባት ሙዚቃ ይከፈት?

**15. ትዕግስት:** እንዴ ከምሽቱ 2 ሰዓት አኮ ሆኗል። እማዬ ሁልጊዜም በዚህ ሰዓት ጎረቤት ትረብሻለሽ ስለምትል ከመሸ ሙዚቃ እንድከፍት አትፈቅድልኝም።

**16.** ምኞቴ: በአዲሱ ቤትሽ ግን የፈለግሽውን ሙዚቃ በፈለግሽው ሰዓት መስማት ትችያለሽ –ለምን ሌሊት አይሆንም!

**17.** ትዕግስት: በጣም አሪፍ!

**18.** ምኞቴ: በዛላይ ጋብቻችንን ማክበር አለብን።

**19.** ትዕግስት: **(confused)** ጋብቻ? ጣቴ ላይ ምንም አይነት ቀለበት አይታየኝም። ምንም እንኳን አብሬህ ለመኖር ብወስንም። ጣቴ ላይ ቀለበት እስካላጠለክልኝ ድረስ ፍቅረኛህ ሆኜ ነው የምቆየው።

**20.** ምኞቴ: ግን ከጥቂት ሰከንዶች በፊት ወ/ሮ ትዕግስት በመባልሽ ደስተኛ ነበርሽ።

**21.** ትዕግስት: የቀልድ ነበራ። በል እባክህ ትንሽ ሙዚቃ ክፈት።

**22.** ምኞቴ: እንደፈለግሽ። ሚስቴቱ

**23.** ትዕግስት: **(firm)** ምኞቴ አቁም፤ እንደዛ ብለህ አትጥራኝ ።

**24. SFX: STEREO SWITCHED ON**

**25. SFX: LOUD MUSIC**

**KW BEGIN**

**26.** ምኞቴ: **(over the music)** ከእኔ ጋ አብረሽ መኖር እንደምትጀምሪ ለእናትሽ ስትነግሪያቸው ምን አሉ?

**27.** ትዕግስት: መጀመሪያ ላይ አልፈለገችም ነበር። ግን በመጨረሻ **(imitates her mother)** “ትምህርት ቤት መሄድ እንደምትቀጥይ ቃል ግቢልኝ እሺ? አለችኝ!

***KW BEGIN***

**28.** ምኞቴ: አሺ፤ ከዛስ?

**29.** ትዕግስት: ከዛማ ወደ ት/ቤት እንደምሄድ ስነግራት ።ትንሽ ቀለላት። እንደዛ ከሆነ አባቴ ለቤት ኪራይ መክፈሉን ይቀጥላል። **(bitter)** አሁን ቤቱን ስለቅላት ፍቅረኞቿን በሙሉ አቤት ድረስ ማምጣት ትችላለች። ቢያንስ አሁን የመጣውን ወንድ ሁሉ አባዬ እያልኩ ለመጥራት አልገደድም።

**30.** ምኞቴ: ሌላስ ምን አሉ?

**31.** ትዕግስት: **(annoyed)** ብዙም ያለችው የለም። ባክህ አሁን ስለሌላ ነገር ብናወራ ይሻላል?

**32.** ምኞቴ: እሺ።

***KW END***

**33. (THEY ARE SILENT, EXCEPT FOR THE MUSIC )**

**34.** ምኞቴ: ነይ ባክሽ ስለነፃነትሽን እንደንስ።

**35.** ትዕግስት: አዎ – እውነትህን ነው እንደንስ።

**36. SFX: SHUFFLING OF FEET AS THEY ዳንኢልCE**

**37. MUSIC FADE OUT**

**<u>SCENE 2: AT THE JUMBES’</u>**

**38. ATMO: AT THE JUMBES’ IN THE EVENING**

**39. SFX: TV RUNNING IN BACKGROUND**

**40. SFX: FUMBLING OF KEYS (HEARD FROM INSIDE)**

**41.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: ንጉሴ? አንተ ነህ?

**42. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**43. SFX: FOOTSTEPS - ንጉሴ ENTERS**

**44.** ንጉሴ: **(indifferent)** ታድያስ እማዬ!

**45.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(angry)** «ታድያስ እማዬ!»ማለትህን ተውና በእዚህ በሌሊት ከየት እንደምትመጣ ብቻ ንገረኝ?

**46.** ንጉሴ: **(timidly)** ይቅርታ እማዬ። ባሴ አርፍዳ ነው።

***KW BEGIN***

**47.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: የምን ባስ?

**48.** ንጉሴ: **(silent)**

**49.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(stern)** ጥያቄ እኮ ነው የምጠይቅህ

**50.** ንጉሴ: ከትምህርት ቤት የምትመጣው ባስ፤ አውቶቡስ

***KW END***

**51.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(even more strict)** አትዋሸኝ አንተ ልጅ። ከትምህርት ቤት እንዲህ አምሽተህ መጥተህ አታውቅም። እንደተባረርክ የማላውቅ መሰለህ?

**52.** ንጉሴ: **(silent)**

**53.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: እዚህ ቦርሳ ውስጥ ምንድን ነው ያለው? ያው የፈረደበት እፅ ነው አይደል?

**54.** ንጉሴ: **(silent)**

**55.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(shouts)** ንገረኝ ምንድን ነው እዚህ ቦርሳ ውስጥ ያለው?

**56.** ንጉሴ: ምንም እማዬ

**57.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(disappointed but calm)** ንጉሴ ሲበዛ ማፈሪያ ነው ያደረከን። ሰው ሁሉ የሚያወራው ስለ ጃለታ እና ዘውዲቱ ልጅ የአደንዛዥ እፅ ሱሰኝነት ነው። እንግዲህ ህይወትህን እንዲህ ከሆነ መምራት የምትፈልገው ቀጥልበት! ቦርሳህን እንኳን አልፈትሽም። ማድረግ ያለብኝን ሁሉ አድርጌያለሁ። ያንተ ውሸት ነው የሰለቸኝ። ዞር በይ አሁን ከፊቴ።

**58. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ዳንኤል IN በለጠ'S ROOM AT NIGHT</u>**

**59. ATMO: NIGHT AT BONGO ACADEMY, INTERIOR**

**60.** በለጠ: **(panting, counts as he does press-ups)** 16, 17, 18 ...

**61. SFX: SOFT KNOCK ON WINDOW**

**62.** በለጠ: **(to himself)** የማነው ደፋር ከማታ ልምምዴ የሚያቋርጠኝ? **(calls)** ማነው?

**63.** ዳንኤል: **(loud whisper from outside)** በለጠ፤ እኔነኝ ዳንኤል።

**64. SFX: WINDOW BEING OPENED**

**65.** በለጠ: **(urgent)** ዳንኤል? ምን እያደረክ ነው?

**66.** ዳንኤል: በለጠ እባክህ እቺ አብድ የሆነች አስተማሪ ሳታየኝ ክፈትልኝ።

**67.** በለጠ: እሺ። በል እጅህን ስጠኝ ። አንተ ስትዘል እኔ እስብሀለሁ እሺ።?

**68.** ዳንኤል: እሺ. 1, 2, 3…

**69. SFX: ዳንኤል JUMPING OUTSIDE**

**70. SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS በለጠ PULLS ዳንኤል INSIDE**

**71.** በለጠ: **(panting)** አንተ ከጠበኩት በላይ ትካበዳለህ።

**72. SFX: WINDOW BEING CLOSED**

**73.** በለጠ: እዚህ ምን ታደርጋለህ? እኔ ደግሞ ወደ ላቦራ ጉዞ ጀምርሃል ብዬ ነበር።

**74.** ዳንኤል: ምንም ገንዘብ የለኝም። አባቴ ደግሞ ስልኩን አያነሳም። ምን እንደማደርግ አላውቅም!

**75.** በለጠ: ግን መግቢያ እንደሌለህ ካወቅ ለምን ሄድክ?

**76.** ዳንኤል: መምህርት ሰብለ የትምህርት ቤቱን ግቢ እንድለቅ የሁለት ሰዓት እድሜ ነበር የሰጠችኝ።

**77.** በለጠ: ግን ገንዘብ እንደሌለህ ልትነግራት ይገባ ነበር። መግቢያ እንደሌለህ ብትነግራት ኖሮ የምታባርርህ አይመስለኝም። አገርህ ምን እየተካሄደ እንደሆነታውቃለች።

**78.** ዳንኤል: አዎ! ግን እዚህ ሀገር የሚኖር አጎት እንዳለኝ ታውቃለች። እሱጋ ሂድ ብላ ነው የላከችኝ። ግን እዛ መሄድ አልፈለኩም። ሀይለኛ ስለሆነ ጭራሽ ነገሮችን ያከብድብኛል።

***KW BEGIN***

**79.** በለጠ: ጆለስ በጣም ነው የተወሳሰበብሽ። እና ምን ለማድረግ ነው ያሰብከው?

**80.** ዳንኤል: እኔም አላውቅም፤ ያንተ ርዳታ ያስፈልገኛል።

**81.** በለጠ: ያራዳ ልጅ፤ ምንም እንኳን አገርህ መመለሻየአይሮፕላን ቲኬት ልገዛልህ ብፈልግም እንንኳን  አልችልም፤ ታውቂያለሽ አይደል።

**82.** ዳንኤል: ኧረ ! እንደዛ አይደለም። **(short pause)**

***KW END*** አባቴን እስከማገኘው ድረስ ብቻ የሆነ መቆያ ቦታ እፈልጋለሁ።

**83.** በለጠ: **(sighs)** እንደዛ ከሆነ ዳኒእዚህ መቆየት ትችላለች። ግን እጅግ በጣም መጠንቀቅ አለብን። ማንም አያውቅም! እሺ? ችግር ውስጥ መግባት አልፈልግም። ቦርሳህ የታል?

**84.** ዳንኤል: አይሮፕላን ማረፊያ ቆልፌበታለሁ።

**85.** በለጠ: እሃ በጣም ድንቅ ! ጥሩ!    እና የኔን ልብስ ለመልበስም ነዋ አላማሽ ?

**86.** ዳንኤል/በለጠ: **(laugh)**

**87. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 4: MORNING AT THE MSOTOS’

**88. ATMO: MORNING IN TANDIKA, INTERIOR**

**89.** ቅዱስ: ምህረት ተነሽ! ትምህርት ቤት ይረፍድብሻል።

**90.** ምህረት: **(stifled crying)**

**91.** ቅዱስ: ምህረት እያለቀሽ ነው እንዴ?

**92.** ምህረት: **(tries to hide it)** አይ ቅዱስ ጉንፋን ሳይዘኝ አይቀርም።

**93.** ቅዱስ: እንደ ወንድማችን ብሩክ አንቺንም TB ያዘሽ ማለት ነው?

**94.** ምህረት: አይ ቅዱስ። ደህና ነኝ። TB አልያዘኝም። እኔ እና እማዬ ሁለታችንም ደህና ነን። ስለዚህ ሀሳብ አይግባህ። ብሩክም መድሀኒቱን ከወሰደ ይሻለዋል። ሀኪሙ እንደዛ ነው ያሉት።

**95.** ቅዱስ: አሁን ተሽሎታል። ሆስፒታል ሄደን ስንጠይቀው ሳል ቀንሶለት ነበር።

**96.** ምህረት: አዎ! ግን ሙሉ በሙሉ አልዳነም። መድሀኒቱን እስኪጨርስ ለ6 ወር ያህል መውሰድ ይኖርበታል።ካቋረጠ በሽታው ተመልሶ ሊመጣ፤ ሊያገረሽበት ይችላል። ከዛ ከእንደገና ሊያስለው እና ህመም ሊሰማው ይችላል።

**97.** ቅዱስ: እየተከታተልኩ በቀን አስር ኪኒን አስውጠዋለሁ ....

**98.** ምህረት: **(laughs)** አይደለም አይደለም ቅዱስ! እንደሱ እንዳታደርግ። ብሩክ ሀኪሙ የፈቀዱለትን ያህል ብቻ ነው መውሰድ ያለበት።

**99.** ቅዱስ: ወዲያው እንዲሻለው ስለፈለኩ እኮ ነው። እስኪድን ገና 6 ወር እንዲጠብቅ አልፈልግም።

**100.** ምህረት: እንደዛ አይደለማ የሚሰራው። ከተፈቀደው በላይ መድሀኒት መዋጥ አደገኛ ነው። ያንን ከተገቢው በላይ መውሰድ ወይንም አላግባብ መድሀኒት መጠቀም፤ ድራግ አቢውዝ ይሉታል። ሊገል ሁላ ይችላል።

***KW BEGIN***

**101.** ቅዱስ: አይደለደም! ውሸትሽን ነው! እኛ እዛ ላቦሪያ እያለን አንዳንድ ጎዳና ላይ የነበሩ ልጆች ድራግ ይሸጡ ድራጎቹ ብሩክ እንደሚወስደው አይነት መድሀኒት አይደሉም። ድራግ መጥፎ ነገር እንደሆነ አውቃለሁ መድሀኒት ነው ጥሩ።

**102.** ምህረት: **(laughs despite the situation)** መድሀኒት ጥሩ ነው። ግን እሱም ቢሆን በአግባቡ ካልተጠቀምከው መጥፎም ሊሆን ይችላል። አንድን ነገር ያለአግባብ ከተጠቀምክ አቢውዚንግ ይባላል። ለዛ ነው ድራግ አቢውዝ የሚባለው።

**103.** ቅዱስ: ስለዚህ መድሀኒት እፅ ነው ማለት ነው?

**104.** ምህረት: አዎ ነው። ግን ፖሊስ መጥቶ አይዝህም **(laughs)** በህግ የተፈቀደ እፅ ነው። ግን ለዛም ነው የዶክተር ፍቃድ የሚያስፈልገው።

***KW END***

**105.** ቅዱስ: ወይኔ! ምህረት በጣም ጎበዝ ነሽ። ጉብዝናን የቦንጎ አካዳሚዎች ናቸው ያስተማሩሽ?

***KW BEGIN***

**106.** ምህረት: **(sad again, sniffs)** ጉብዝናን አትማርም። ስትወለድም ጎበዝ ነህ። ግን ማንኛውም ሰው ትምህርት ቤት በመሄድ ነገሮችን መማር ይችላል።

**107.** ቅዱስ: እማዬ ገንዘብ ስታገኝ እኔና ብሩክም ትምህርት ቤት እንሄዳለን። እና ነገሮችን ተምሬ እንደ አንቺ ጎበዝ እሆናለሁ።

***KW END***

**108.** ምህረት: **(sniffs more)** ወይ ቅዱስ…

**109. SFX: DOOR OPENS**

**110. STEPS - ወ/ሮ ሉሊት APPROACHES**

**111.** ወ/ሮ ሉሊት: ምህረት! አሁንም እዚህ ነው ያለሽው። ወደ ት/ቤት የሄድሽ እኮ መስሎኝ ነበር። እባክሽ እስኪ. ይህንን እንስራ ከጀርባዬ ላይ አውርጅልኝ።

**112.** ምህረት/ወ/ሮ ሉሊት **(THEY ACT LIFTING HEAVY STUFF)**

**113. SFX: WATER CONTAINER PUT DOWN**

**114.** ወ/ሮ ሉሊት: ለምንድን ነው ትምህርት ቤት ለመሄድ ያልተዘጋጀሽው? አረፍዶብሽ የለ?

***KW BEGIN***

**115.** ምህረት: እማዬ... አልሄድም።

**116.** ወ/ሮ ሉሊት: ለምን? እንደማትሄጂ ባውቅ ኖሮ እንደዚህ በጠዋት ውሃ ልቀዳ አልሄድም ነበር።በዚህ በታመመ ጀርባዬ ደህና አንቺን የምልክሽን።

**117.** ምህረት: እማዬ... ከእንግዲህ ት/ቤት መሄድ አልችልም።

**118.** ቅዱስ: በቃ በደንብ ጎበዝ ሆነሻል ?

**119.** ወ/ሮ ሉሊት: ምን? ለምን? አንቺው አልነበርሽ እንዴ ነጋ ጠባ ትምህርት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ስትነግሪኝ የነበርሽ? እኔ ትምህርቴን ባለመጨረሼ ያለፍኩበትን ልጄ ሲገጥማት ማየት አልፈልግም።

***KW END***

**120.** ምህረት: እማዬ... ርዕሰ መምህርቷ አሰናብተውኝ ነው። .... ለምን እንደሆነ ታውቂያለሽ።

**121.** ወ/ሮ ሉሊት: **(shocked)** ኧረ በፍፁም!

**122.** ቅዱስ: እማዬ? ማሰናበት ምን ማለት ነው?

## 123. OUTRO - NARRATOR

በሉ « መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የተሰኘው ድራማ የዛሬው ጭውውት እዚህ ላይ ያበቃል። ምህረት ሁልጊዜም ትምህርት ቤት መሄድ ያስደስታት ነበር። ታድያ አሁን ትምህርት ቤት መሄድ ካቆመች በኋላ እንዴት ልትወጣው ይሆን? ትዕግስት እና ዳንኤልስ አዲሱን መኖሪያ ይላመዱታል? የዳንኤልን ነገር ካነሳን አይቀር ወደ ሀገሩ ላቦሪያ መመለስ አይችልም። ነገሮች ሁሉ የተረጋጉ አይደሉም፤ አገሩ በሙሉ በወታደር ተከቧል። በእርግጥም ይህ ብዙ ወጣት ልጆች ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል። ከዳንኤል ጋር ከቅርብ ጓደኝነትም ባለፈ ቀረቤታ ያላት አልማዝ በውስጧ የሚመላለሰውን በቪዲዮ ዘገባዋ ታካፍለናለች dw.de/lbe የድረ ገፅ አድራሻችን ነው። እዚሁ ድረገፅ ላይ ከዚህ ቀደም የተላለፉትን « መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የተሰኘውን ድራማ ጭውውቶች በድጋሚ መስማት ይቻላል። ታሪኩ እንዴት እንደሚቀጥል ለማወቅ በሚቀጥለው ጊዜ ራዲዮ መከታተሉን እንዳትረሱ። ለዛሬው ደህና ሁኑ!